# በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተደረገ ማሻሻያ፣

## ከዚህ በፊት በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ ማሻሻያ፣ በሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ እንዲፀድቅ የሚቀርብ ማሻሻያና በደንቡ ላይ የተደረገ ዕርማት

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

August 12, 2022

# በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች

## ነሐሴ 22 ቀን 2013 ዓ.ም. የፀደቀ ማሻሻያ

### ነባሩ

አንቀጽ 5.7. መንግሥት አክሰስ አልሲዮን ማኅበር የተባለውን አፍርሶ ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ከሃይማኖት አባቶች፣ ከሲቪል ማኅበራት፣ ከሙያ ማኅበራት እና ከማኅበሩ አባሎች ውስጥ ቢያንስ ሶስት ግለሰቦች የተካተቱበት ተቆጣጣሪ የሆነ የጊዜያዊ ሞግዚት ባለአደራ ቦርድ እንዲቋቋም በማድረግ በዚሁ ባለአደራ ቦርድ የበላይ ቁጣጣሪነት ቤት ገዢዎች ንብረታቸውን እንዲያገኙ እንዲያመቻች።

### የተሻሻለው

አንቀጽ 5.7. አክሰስ ሪል ኤስቴት በማናቸውም ምክንያት እንዲፈርስ ቢወሰን ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም የሃይማኖት አባቶች፣ ከሲቪል ማኅበራት፣ ከሙያ ማኅበራት እና ከማኅበሩ አባላት ቢያንስ ሶስቱ የተካተቱበት ተቆጣጣሪ የሆነ ጊዜያዊ የሞግዚት ባለአደራ ቦርድ እንዲቋቋም በማድረግ በዚሁ ባለደራ ቦርድ የበላይ ተቆጣጣሪነት ቤት ገዥዎች ንብረታቸውን እንዲያገኙ እንዲያመቻች።

## ነሐሴ 14 ቀን 2014 ዓ.ም. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚርብ የማሻሻያ ሐሳብ

### ነባሩ

አንቀጽ 12.5.1 አዲስ አበባ ውስጥ በቋሚነት የሚኖሩ፤

### የተሻሻለው

አንቀጽ 12.5.1. ለፕሬዚዳንትነት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትነት፣ ፀሐፊነት፣ ሂሳብ ሹምነትና፣ ገንዘብ ያዥነት አዲስ አበባ ውስጥ በቋሚነት ከሚኖሩ አባሎች መካከል መመረጥ ይኖርባቸዋል። የሕዝብ ግንኙነት እና አባል ግን ነዋሪነታቸው ውጭ አገራት ከሆኑ አባሎች መካከል ሊመረጡ ይችላሉ።

# ነሐሴ 14 ቀን 2014 ዓ.ም. ዕርማት

## ነባሩ

አንቀጽ 23.6. የማኅበሩ ሥራ ቀጣይነት ለማረጋገጥና ለመከታተል ይቻል ዘንድ የመጀመሪያው ኮሚቴ አባሎች የሥራ ዘመን እንደተጠናቀቀ ግማሾቹ ብቻ (ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ገንዘብ ያዥና የሕዝብ ግንኙነት ኦፊሰር) በአዲስ ተመራጮች እንዲተኩ ይደረጋሉ። ቀሪዎቹ (ፕሬዚዳንት፣ ፀሐፊ፣ ገንዘብ ያዥና አንድ አባል) ለተጨማሪ አንድ ዓመት ካገለገሉ በኋላ በሌሎች ተመራጮች ይተካሉ።

## የታረመው

አንቀጽ 23.6. የማኅበሩ ሥራ ቀጣይነት ለማረጋገጥና ለመከታተል ይቻል ዘንድ የመጀመሪያው ኮሚቴ አባሎች የሥራ ዘመን እንደተጠናቀቀ ግማሾቹ ብቻ (ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ገንዘብ ያዥና የሕዝብ ግንኙነት ኦፊሰር) በአዲስ ተመራጮች እንዲተኩ ይደረጋሉ። ቀሪዎቹ (ፕሬዚዳንት፣ ፀሐፊ፣ ሂሳብ ሹም አንድ አባል) ለተጨማሪ አንድ ዓመት ካገለገሉ በኋላ በሌሎች ተመራጮች ይተካሉ።